የቡረጋርድ ዕቅድ፣ የማሕበረሰቡን የወደፊት ኑሮ መቅረጽ

WWW.ALEXANDRIAVA.GOV/BEAUREGARDPLAN

ነዋሪዎች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ማሕበራዊ ድርጅቶች፣ በአቅራቢያው ያሉ ሲቪክ ቡድኖች እና ባለንብረቶች በቀጣይ 20 እና 30 አመታት በቡረጋርድ አካባቢ ሊታይ የሚችለውን የእድገት ራዕይ ለመፍጠር ከከተማው ጋር ከአንድ አመት በላይ ሲሰሩ ቆይተዋል። ይህ የማህበረሰቡ ራእይ የቀረበውን ዕቅድ በማዘጋጀቱ ላይ ውሏል።

ዕቅዱ (ፕላኑ) ምንን ያስፈጽማል፤

በሰዎችና በሚያዘወትሩዋቸው ቦታዎች መካከል አመቺ መገናኛ መንገዶችን መፍጠር፤ ነዋሪዎች ፈጣን ወደ ሆነው የትራንስፖርት ጣቢያ፣ አዳዲስ የምግብ ሽቀጣሽቀጥ ሱቆች፣ ፓርኮችና ፕላዛዎች፣ የቢሮ ሕንጻዎች፣ እና ብዙ የሽቀጣሽቀጥ ቦታዎች በሰባት ደቂቃ ወይም ባነሰ ጊዜ በእግር ይደርሳሉ። በቡረጋርድና ሳንገር መንዶች መገናኛ የሚሰራ አዲስ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ ፈጣን የድንገተኛ አደጋ ምላሽ በመስጠት የተሻለ የሕዝብ ደህንነት ለከተማው ምዕራባዊው ጫፍ ይሰጣል።



ልብ ይበሉ፡ የሕንፃዎቹ ምስል ለገለፃው በሚመች መጠን የተዘጋጀ እንጂ ትክክለኛ መጠኑን የሚወክል አይደለም

የአካባቢው ትራፊክ (ተሽከርካሪ መዟዟር) ማሻሻልና የትራፊክ መጨናነቅን መቀነስ። በቡረጋርድ አካባቢ የመንገዶች መሻሻልና ተጨማሪ መተላለፊያ መንገዶች መኖር የትራፊክ መጨናነቅን ይቀንሳል። ሰፋ ያሉ የእግረኛ መንገዶችና መሻገሪያዎች ለእግረኞችና ለብስክሌት ተጠቃሚዎች ምቹ አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ለተወሰነ አገልግሎት የተመደቡ የመንገድ መስመሮች (ለይንስ) አስተማማኝና ብቃት ያለው የመተላለፍ አገልግሎት ይፈጥራሉ። በመጓጓዣ መሻሻል፣ በተጨማሪ መኖሪያ ቦታዎች፣ ቢሮዎች፣ እና በሁሉን-አቀፍ እድገት ምክንያት ቡረጋርድ አዲስ የተለየች ስፍራ ትሆናለች።

ደዲከትድ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች መፍጠር፤ በጸደቀው የቡረጋርድ ፕላን መሰረት ያረጁ የአፓርትመንት ሕንጻዎችን በ30 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በአዳዲስ መቀየር፤ በግምት 800 የሚሆኑ የፈረሱ ቤቶች ተመጣጣኝ በሆኑ ኮሚትድ እና ዎርክፎርስ ሀውሲንግ ይተካሉ። በሽግግሩ ወቅትም የከተማው ቢሮ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ከቦታ ለውጥ ጋር የተያያዘ ትርጉም ያለው አገልግሎትና እርዳታ እንዲያገኙ ከአልሚዎች ጋር ይሰራል።

በከተማና በተፈጥሮአዊ አከባቢዎች ቀጣይነት ያለው ሽግግር መፍጠር። አብዛኛዎቹ አዳዲስ ቤቶች በአጠ ቃላይ ከአከባቢው መናፈሻዎች ወይም አዳዲስ ክፍት ቦታዎች ከእሩብ ማይል በማይበልጥ ርቀት ውስጥ ይሆናሉ። ማህበረሰቡ እቤቱ አጠገብ እየተሰባሰበ የአካል እንቅስቃሴ ለማድረግ፣ ስፖርት ለመጫወት፣ እንዲሁም እውጭ ለመዝናናት አዲሱ የአትሌቲክስ ሜዳ፣ የእግረኛ መንገዶች፣ መንሸራሸሪያ መንገዶች እና የብስክሌት መንገዶች ግንኙነት ሆነው ያገለግላሉ። አዲሶቹ ቤቶች ኤነርጂ (ሃይል) ቆጣቢና ለአከባቢው ተስማሚ ሆነው የሚሰሩ ይሆናሉ።

በሚጸድቀው ዕቅድ መሰረት የቡረጋርድ ግንባታ እነዚህን ያካትታል።

- እቅዱ ከልማት ድርጅትና ከከተማ መዋጮ ለእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለክፍት ቦታ፣ ለተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች፣ ለመረት ይዞታ ማስተካከያና ለዛፍ ማሳመርያ አላማ የሚመደብ $210 ሚሊዮን ገንዘብ ይጠይቃል።
- የገበያ ቦታዎች፣ ቢሮዎች፣ ሆቴል፣ እና መኖሪያ ቤቶች እርስ በርስ የተገናኙና በተቀናጀ መልኩ በህዝብ ትራንስፖርት መስጫ ጣቢያዎች አከባቢ የሚሰሩ ይሆናሉ።
- ብዙ የምግብ ቤት ምርጫዎች፣ አዲስ የምግብ ሸቀጣሸቀጥ መደብር፣ እና አሁን ያሉትን የምግብ ሸቀጣሸቀጥ መደብሮች የሚያስፋፋ የሰፈሩ የገበያ ቦታ ያለው
- ከ800 በላይ አዳዲስ ደዲከትድና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ተሰርተው አሁን ካሉት ውስጥ 32% መኖሪያ ቤቶቹን ይተካሉ።
- ለሰፈሩ የተሻለ ፈጣን የምላሽ ጊዜ የሚኖረው አዲስ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ
- በሰሚናሪ መንገድና በቡረጋርድ መንገድ መገናኛ ላይ የተሻሻለ መተላለፊያ
- ከግንባታው ጋር የተቆራኘ ፈጣንና ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት
- አዳዲስ የወስጥ ለውስጥ መንገዶችና የእግረኛ መሄጃ በመስራት ትራፊኩን ማከፋፈል
- የበለጠ ክፍት ቦታና ለማህበረሰቡ መዝናኛ የአትሌቲክስ ሜዳ
- ወደ ትምህርት ቤቶች የሚያስከዱ የተሻለ እይታ ያላቸው የእግረኛ መንገዶች

የቡረጋርድ ዕቅድ ካልጸደቀ ምን ይሆናል?

- ባለው ህግ መሰረት ግንባታው ወደፊት ይሰራል፣ ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ በግል ለሚሸፈኑት የትራንስፖርት ማሻሻያዎች፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች፣ ማህበራዊ ደህንነት፣ የሽቀጣ ሽቀጥ መደብሮችና መናፈሻዎች ማሰሪያ ከ210 ሚሊዮን ዶላር በላይ ያጣል።
- ግንባታው በተቀናጀ መንገድ ሳይሆን በዘፈቀደ የሚሰራ ይሆናል።
- አሁን ያሉት ክፍት ቦታዎች፣ መናፈሻዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ እና ሰፈሮች የታቀደላቸውን የእርስበርስ ማገናኛዎችን ያጣሉ።
- አዳዲስ የሽቀጣሽቀጥ መደብሮችና ምግብ ቤቶች ለመኖራቸው ዋስትና የለም።
- አዳዲስ የከተማ ቤቶችና ኮንዶሚኒየሞች ተመጣጣኝ ዋጋና የደዲከትድ መኖሪያ ቤትነት ዋስትና አይኖራቸውም።
- ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት ወይም ከዛ በላይ አዲስ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ ስለማይኖር በማህበራዊ ደህንነት ላይ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል።
- የተጨናነቀ ትራፊክና ደካማ የአውቶቡስ አገልግሎት ይኖራል።
- የትራንስፖርት ማሻሻያው ከግንባታው ጋር ካልተቀናጀ የሰፈሩ አገልግሎት በየግል አካሄድ ላይ የተመሰረተ ይሆናል።
- አዳዲስ መናፈሻዎች ወይም ክፍት ቦታዎች አይኖሩም፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ዛፍ ይጠፋል።



የቡረጋርድ ‘ስሞል ኤሪያ ፕላን’ (መለስተኛ የአከባቢ ዕቅድ) የመጀመሪያ ረቂቅ ሃሳብ እንዲሰጥበት በኢንተርነት ወይም በሲቲ ሆል ቁጥር 1900 ክፍል፣ በበርክ ቤተመጻሕፍትና በቢትሊይ ቤተመጻሕፍት ገብጇል ሆኗል። ከተማውና ማህበረሰቡ ዕቅዱን ለማሻሻል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ የሕዝቡም አስተያየት ቢጨመር ይበረታታል።

WWW.ALEXANDRIAVA.GOV/BEAUREGARDPLAN